# አቶ መለስ እና ግብፅ

አስራት አብርሃም

የፖለቲካን ሀ ሁ ሳልጀምር፥ ገና በልጅነት ወራት ሳለሁ ገጣሚ ለመሆን ነበር ምኞቴ፡ ምኞት አይቀርም መቼም፤ እናም ይህን ፅሁፍ በግጥም እጀምረው ዘንድ ፍላጎቴ ሆነ!

*ሀበሻ በሙሉ*
*ደሙን ቢመረመር*
*ግብፅን የሚያስጠላ*
*አንዳች ንጥረ ነገር*
*ይገኝበት ነበር፡፡*

ከታሪካችን በመነሳት ግብፅ እና ኢጣሊያ በጣም የምንጠላ ሀበሾች በጣም ብዙ ነን፡፡ እነዚህ አገሮች ሲነሱ ደማችን ነው የሚሞቀው፡፡ ሲተናኮሱንማ

“ኧረ ጎራው፥ ኧረ ጎራው…” ማለቱን ነው የሚቀናን፡፡ የአባቶቻችን ታሪካዊ ገድልና ጀግንነት በማስታወስ!

የኢህአዴግን ሰዎች በተለይ አቶ መለስን ግን በዚህ አልጠረጥራቸውም፡፡ አቶ መለስ ለሮይተርስ ሰጡት በተባለው አነጋጋሪ ቃለ ምልልስ ላይ “ግብፅ እኛን ልትወር ብትመጣ የጉራዕን ጦርነት መልሰን እናሳያታለን” አሉ ሲባል ሰምቼ “አበጀህ የእኛ ልጅ!” ልላቸው ዳድቶኝ ነበር፡፡ ከዚያ በፊት ግን ጥያቄ መጠየቅ መረጥኩ፡፡ “እውነት ግን ግብፅ እኛን ልትወረን ትችላለች?” የሚለው ነው የመጀመሪያው ጥያቄ!

አልመሰለኝም፡፡ ያው እንደተለመደው ፀረ ኢትዮጵያ የሆኑ ኃይሎችን ትረዳ ይሆናል እንጂ ደፍራ ጦሯን ልታዘምትብን ትችላለች ብዬ ለማሰብ የሚያስችለኝ በቂ ምክንያት አላገኘሁም፡፡ ልትወረን ብትነሳ ግን “ጠበንጃዬን ስጡኝ” ብለው ከሚነሱትና ለአገራቸው ሉአላዊነት ፊት ከሚሰለፉት ኢትዮጵያውያን ውስጥ አንዱ እንደምሆን ምንም ጥርጥር የለውም፡፡ በእርግጥ በአቶ መለስ አመራር ስር ሆኖ መዋጋቱ አደጋ አይኖረውም አይባልም፡፡ ብዙ መስዋዕትነት ተከፍሎ ጠላት መመከት ከተቻለ በኋላ የባድሜን ዓይነት ክህደት መጨረሻ ላይ ሊያጋጥም ይችላል፡፡ እንደ ሚታወቀው በኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ውጊያውን አሸንፈን ነበር፡፡ አቶ መለስ ከዚያ በኋላ በተደረገው የአልጀርሱ ስምምምነት ላይ የህዝቡን አስተያየትና እምነት ወደ ጎን ትተው፥ በራሳቸው መንገድ ሄደው፥ የግልግል ዳኝነት በሄግ እንዲቋቋም ተስማምተው በውጤቱ ተሸናፊ እንድንሆን የተደረግንበት አሳዛኝ አጋጣሚ መቼም የሚረሳ አይደለም፡፡

ወደ ዋናው ርዕስ ልመለስና ግብፅ ኢትዮጵያ ልትወር እንደማትችል ግልጽ ነው፡፡ ታዲያ ይህ አቶ መለስ በግብፅ ላይ ያሰሙት ከረር ያለ አነጋገር ከምን የመጣ ነው ብሎ መጠየቅ ያስፈልጋል፡፡ ይህ ሁለተኛው ጥያቄዬ ነው፡፡ አንድ ነገር አለ መካድ የማይቻል፡፡ ይህም ግብፅ የትጥቅ ትግል የሚያካሄዱትን የኢትዮጵያ ኃይሎች ልትረዳ ትችላለች የሚል ስጋት አቶ መለስ እንዳላቸው ነው፡፡ “ግብፅ የኢትዮጵያን አማፂያን እንደምትረዳ ተጨባጭ ማስረጃ አለን፡፡ ያለን ማስረጃና የትኛውን ቡድን በምን መልኩ እንደምትረዳ ጊዜው ሲደርስ ይፋ እናደርጋለን” ማለታቸው ይህን የሚያረጋግጥልን ነው፡፡

እንደ ዛሬ አያድርገውና አቶ መለስ ድሮ በሽፍትነት ዘመናቸው ክላሽንኮቫቸውን ተደግፈው፥ ቁጭ ብለው፥ ሪዛቸውን እያሻሹ ጥይትና ስንቅ ሊያቀብሏቸው ሚችሉትን አገሮች ሲያስቡ ወደ አእምሯቸው ቀድመው ከሚሙጡት አገሮች ግብፅ ቀዳሚ ነበረች፡፡ በተለይ የኤርትራን መገንጠል ግቡን እንዲመታ ከጅምሩ አንስቶ ኤርትራዊያን ወጣቶች በማስጠጋት፣ በማሰልጠንና የራሳቸው ሬድዮ ጣቢያ እንዲኖራቸው በማድረግ፥ ከዚያም አልፋ ጀብሀን በማቋቋሙ ሂደት የተጫወተችውን ሚና አድንቀው አይጠግቡም ነበር ይባላል፡፡ እስከ ቅርብ ድረስም ግብፅ “በጣም ወዳጅ አገር” ነበረች ለአቶ መለስ!

በዚህ ምክንያትም ይመስላል የግብፁ ፕሬዝደንት ሁስኒ ሙባረክ ይህን የአቶ መለስን ድንገተኛ መግለጫ ሲሰሙ፥ “በሁለታችን መሀል በጣም ጠንካራ የሆነ ግንኙነት ያለን በመሆኑ ከአቶ መለስ በኩል የተሰነዘረውን ውንጀላ እጅግ አስደንግጦኛል” ያሉት፡፡ የግብፁ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አህመድ አቡል ገሃር በበኩላቸው “እኛ ጦርነት አንፈልግም፡፡ ጦርነትም አይኖርም፡፡ በቃለ ምልልሱ ላይ አቶ መለስ የተጠቀሙበት አነጋገር ግን አስገርሞኛል” ብለዋል፡፡

አዎ! የዛሬ አያድርገውና አቶ መለስ እና ሁስኒ ሙባረክ ወዳጆች ነበሩ፡፡ አሸባሪዎች አዲስ አበባ ላይ የግብፁን ፕሬዝዳንት ለመግደል ሙከራ ባደረጉበት ወቅት ይህን ሙከራ ካቀነባበሩት ውስጥ አንዱ ወደ ሱዳን በመሄዱና ሱዳንም አሸባሪውን አሳልፋ ለመስጠት ፍቃደኛ ባለመሆኗ በኢትዮጵያና በህዝብዋ ላይ ሊያስከትል የሚችለውን ጉዳት ከግምት ውስጥ ሳያስገቡ የሱዳን ዜጎች ሁሉ በሃያ አራት ሰዓት ውስጥ ኢትዮጵያን ለቀው እንዲወጡ አዋጅ አስነግረው ነበር፡፡ በወቅቱ ሱዳን ተመሳሳይ እርምጃ ወስዳ ቢሆን ኖሮ በሱዳን ውስጥ ይኖሩ የነበሩት በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን ዕጣ ፈንታ ምን ሊሆን ይችል እንደነበረ መገመት አይከብድም፡፡ በኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት መነሳት ምክንያት ብዙ ዜጎቻችን ኤርትራ ውስጥ ቀልጠው ቀርቷል፡፡ እንዲያ የሆነው በወቅቱ የኢትዮጵያ መንግስት አስቀድሞ ሳያስጠነቅቃቸው በመቅረቱ  ነው፡፡ በሱዳን ላይ የተወሰደው እርምጃም ለአጭር ጊዜ የቆየ ቢሆንም በቅድሚያ ለአገሩና ለዜጎቹ የሚያሰብ መንግስት ወይም መሪ የሚወስደው እርምጃ ዓይነት አልነበረም፡፡ ያልተመከረበት፤ ችኩል ውሳኔ ነበር፡፡ በወቅቱ ብዙ ሱዳናዊያንም አሳዝኗል፡፡ እንዲያም ሆኖ ከግብፅ በወቅቱ ምስጋና አላገኙበትም፡፡ ወዳጅነቱን ግን ቀጥሎ ነበር፡፡ ዛሬን ግን ያ የአቶ መለስ እና የሁስኒ ሙባረክ ፍቅር ከቦታው እንደሌለ ግልፅ ሆኗል፡፡ የወዳጅነት ፅዋው ተደፍቷል ማለት ነው፡፡

አንዳንድ የትጥቅ ትግል ለማካሄድ የሚፈልጉ ተቀዋሚዎች በተለይ “ግንቦት ሰባት” ከግብፅ ጋር ውስጥ ለውስጥ ግኑኝነት ጀምሯል መባሉ፤ ሱዳንና ግብፅ አዲሱን የአባይ ውሀ አጠቃቀም ስምምነት ተቀብለው ያለመፈረማቸው ጉዳይ፤ ግብፅ ከኤርትራ መንግስት ጋር የነበራትን ግንኙነት የማደስ ፍላጎት ማሳየቷ፡፡ የዊኪሊክስ ድሕረ ገፅ ደግሞ ግብፅ የደቡብ ሱዳን ሪፈረንደም መካሄድ ስጋት ላይ እንደጣላት መግለፁ፤ በዚህም ምክንያት በአባይ ተፋሰስ አገሮች ዘንድ የሚኖረው የኃይል አሰላለፍ ላይ የሚኖረው አንድምታ ይህ ሁሉ ይኖራል፡፡ ከዚህ በመነሳት ግብፅ በሰሜኑ ሱዳንና በኤርትራ መንግስት ላይ የራሷን ትፅዕኖ ልታሳድር እንደምትችል ምንም ጥርጥር የለውም፡፡ ግብፅ ኢትዮጵያ ላይ ጫና ለመፍጠርና በአባይ ወንዝ ላይ ያላትን የበላይነት ለማስጠበቅ ካላት ፍላጎት በትጥቅ ትግል የተሰለፉትን ኢትዮጵያውያን ወደ ጎንደርና ጎጃም በቀላሉ መሸጋገሪያ መንገድ እንዲያገኙና የእርስ በእርስ ጦርነቱ እንዲፋፋም የማይተካ ሚና ልትጫወት ትላለች፡፡ ያ ከሆነ ደግሞ ስጋቱ ለአቶ መለስ ግልፅ ነው፡፡ “ምሽጌ ነው” የሚሉት የአራት ኪሎው የምኒልክ ቤተ መንግስት እንደበፊቱ አስተማማኝ አይሆንም፡፡ እንጂማ ግብፅ የኢትዮጵያን መንግስት ተቀዋሚዎች ከመርዳት መቼ ተቆጥባ ታውቃለች! ራሳቸው አቶ መለስም ጨምሮ የዕድሉን ተቋዳሽ ሆነው ነው ለስልጣን የበቁት፡፡ ዛሬ ግን እርሷ ባልፈለገችው አቅጣጫ መጓዝ መጀመራቸውን ስትረዳ ዝፏናቸው ላይ አነጣጠረች፡፡ እርሳቸውም የዋዛ ሰው አይደሉም፡፡ “አሁን ገና በዓይኔ መጣሽ” ብለው ኢሳይያስ አፈወርቂን የቀጠቀጡበት ኢትዮጵያዊ ዱላ አንስተው እያስፈራሩ “አርፈሽ ብትቀመጪ ይሻልሻል” እያሏት ነው፡፡ ግን እውነት አቶ መለስ ከግብፅ በኩል ጦርነት እንዳይሰነዘርባቸው ፈርተው ነው! እንዲያ ቢሆን ኖሮ እስካሁን ዝም አይሉም ነበር፡፡ ድንገት ተነስተውም በሚዲያ መግለጫ ባልሰጡ! በመጀመሪያ ውስጥ ለውስጥ ነበር የሚደራደሩት፡፡ የዲፕሎማሲ ሥራው ካይሮ ድረስ እየተመላለሱ ያካሄዱ ነበር፡፡ ልክ ከኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት በፊት ከኤርትራ መንግስት ጋር እንዳደረጉት ማለት ነው፡፡

ምክንያቱ ያ ካልሆነ አቶ መለስ ከግብፅ ጋር ሰጣገባ ውስጥ ለመግባት የመርጡበት ሌላ ምክንያትም አላቸው ማለት ነው፡፡ በኢትዮጵያ ህዝብ ዘንድ በጣም የሚታሙበት በአገር ጉዳይ፣ በሉኣላዊነት ላይ የመደራደር አሳፋሪ ታሪካቸውን መጨረሻ ላይ ለማስተካከል ፈልገውም ሊሆን ይችላል፡፡ ይህ ከሆን ምክንያቱ እሰየው የሚያስብል ነው፡፡ በነገራችን ላይ አሁን የኢትዮጵያ መንግስት በአባይ ጉዳይ ላይ የያዘው አቋም የሚደገፍ ነው፡፡ አቶ መለስ “ከተለያዩ አማፂያን የሚነሱትን ጥያቄዎች የኢትዮጵያ መንግስት ለመመለስ ከቻለ ልዩነታችን ማዕከላዊ ቦታ ስለሚያገኝ ችግራችንን መፍታት እንችላለን፡፡ ስለዚህ ግብፆች በተረበሸ ውሀ ውስጥ አሣ ማጥመድ አይችሉም፡፡ ምክንያቱም አሣው ስለማይኖር ነው፡፡” ማለታቸውም ተዘግቧል፡፡ በእውነቱ ይህ የአቶ መለስ አባባል ከልብ ከሆነ በጣም የሚደነቅ ነው፡፡  ነገር ግን የሰከነ የዲፕሎማሲያዊ ስራ ከመስራት ይልቅ ከግብፅ ጋር የጀመሩት የሚዲያ ጦርነት

አስፈላጊ አልነበረም፡፡ ለዚህ ነው ይህ የአቶ መለስ የአቋም ለውጥ "ከልብ ላይሆን ይችላል" የሚል ጥርጣሬ በስፋት እየታየ ያለው፡፡

ሌሎች አገራዊ አጀንዳዎች፣ የዴሞክራሲና የሰብአዊ መብቶች ጥያቄ ለማስቀየስና ህዝቡ ለለውጥ የጋራ ትግል እንዳያካሄድ ለማድረግ፣ ውዥንብር ውስጥ ለመክተት ተብሎ የተዘጋጀ ሴራ ሊሆን ይችላል፡፡ አቶ መለስ ከጫካ ጀምሮ "ጭር ሲል አልወድም" የሚል ፍልስፍና እንዳላቸው በተለያየ ወቅት ከእርሳቸው ጋር ቅርበት የነበራቸው ሰዎች ይናገራሉ፡፡ አረጋዊ በርሄ በወቅቱ በነበረው የህወሀት ሕገ ደንብ መሰረት "በውጊያ ላይ እያለ የሸሸ ታጋይ ይገደላል" በሚለው ሞት በይኖባቸው በአቶ ስብሀት ነጋ ልመና ከተረፉ ወዲህ የፖለቲካው ጨዋታ የህልውናቸውም ጉዳይ ሆኗል፡፡ በስልጣናቸውና በህልውናቸው ላይ ከየትኛውም አቅጣጫ ከውስጥም ከውጭም ማለት ነው ሊቃጣባቸው ከሚችል ማንኛውም ዓይነት ጥቃት አስቀድሞ ለመከላከል፤ ከዚያም በአሻገር ከእርሳቸው በተቃራኒው ወገን ያለው ኃይል ተረጋግቶ እንዳያስብና እሳቸውን ለማሸነፍ ዕድል እንዳያገኝ ለማድረግ ሁሌም የማስቀየስና የማምታታት ሥራ እንደሚሰሩ ይነገራል፡፡

በየጊዜው በሚፈጥሯቸው ተከታታይ የሆኑና እጅግ በርካታ ችግሮች ሌላው እንዲጠመድ፥ ከእውነተኛው ጥያቄና ትግል ውጭ እንዲሆን በማድረግ ስልጣናቸውን በቀላሉ ማስጠበቅ የሚችሉበት ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡ ከዚያም አልፈው ስልጣናቸውን በዘላቂነት ለማስቀጠል የዘመድ፥ የጓደኛ፥ የጥቅም፥ የወንዝ ልጅነትና ሌሎም ግኑኝነቶች በመዘርጋት በዙሪያቸው በየደረጃው የተለያዩ የከለላ ምሽጎችን አበጅቷል፡፡ ይህ አሰራር ለዘመናት ሲጠቀሙበት የኖሩ በመሆናቸው ለሁሌም ተጠራጣሪ፥ አጥቂ እና አደርባይ የሆነ ሰብእና እንዲኖራቸው አስተዋፅኦ አድርጓል" የሚሉ አሉ፡፡ በዚህም ምክንያት ለስልጣናቸውና ለህልውናቸው ሲሉ አንዳንዴ ወደ ገበያ የማያወጡት ነገር የለም፡፡ በሁሉም ነገር ላይ፥ በአገር ጉዳይ ሳይቀር ለመደራደር ቸር ሆነው የሚገኙበት ጊዜ አለ፡፡ ሌላ ጊዜ ደግሞ በቀላሉ መፍታት በሚቻልበት ጉዳይ ላይ ሳይቀር ግትር ይሆኑና ብዙ ነገር እንዲበላሽ ያደርጋሉ፡፡ ይህ ሁሉ የሚሆነው ከግል ጥቅማቸው አንፃር ነገሮች ሁሉ ስለሚያዩ ነው፡፡ መቼም አቶ መለስ እንደነ አፄ ቴዎድሮስ ወይም እንደነ አፄ ዮሐንስ "ከአገሬ በፊት አንገቴን ልስጥ" የሚሉ አይደሉም፡፡ እርሳቸው ከሌሎቻችን የተለየ የአገርነት ፍልስፍና እንዳላቸው ይታመናልና ነው፡፡ በዚህ ምክንያትም አንገታቸውን ለአገር ሊሰጡ ይቅርና ስልጣን ለማግኘት ሲሉ የአገሪቷን አንገት ቆርጠው በሰሀን ከማቅረብ ወደኋላ እንደማይሉ በኤርትራ ጉዳይ ላይ በደንብ አስመስክሯል፡፡

ስለዚህ አሁን ከግብፅ ጋር የጀመሩት አዲስ የሚዲያ ጦርነት አንዳች ጥቅም የሚያስገኝላቸው ሆኖ ስለታያቸው ሊሆን ይችላል፡፡ ይህን ግላዊ ጥቅም በደንብ አስልተው የገቡበት ጉዳይ ላለመሆኑ ምን ማረጋገጫ አለን? ብሎ መጠየቁ ብልህነት ነው የሚሆነው፡፡

አንዳንዴ ስለአገራችን ጉዳይ ሳስብ በጣም አዝናለሁ፡፡ የራሳችንን መሪ ይህን ያህል ለመጠርጠር ባንገደድ በጣም ጥሩ ነበር፡፡ ነገር ግን እኛ አልታደልንም፡፡ የምናምነው መሪ አላገኘንምና ሁሌም በሚሆነው ነገር ሁሉ እንጠረጥራለን፡፡

---

*አስራት አብርሃም አድናቆትን ካተረፈው **"ከአገር በስተጀርባ"** የተሰኘው መጽሐፍ ወጣት ደራሲ ነው።*